

# የብፅእና ስብከቶች

ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ለማየት መጥተው ነበር። ወደተራራም ወጥቶ ወደእርሱ የሰበሰባቸውን ደቀመዛሙርቱን ማስተማር ጀመረ። እንዲህም አስተማራቸው።

*"በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁአን ናቸው፤ የእግዚአብሔር መንግስት የእነርሱ ናትና።"*
እንዲህ አይነት ሰዎች ትሁታንና ራሳቸውን ከፍ ከፍ የማያደርጉ ናቸው። ኢየሱስ አንድ ጊዜ ራሱን እንደሕፃን ዝቅ የሚያደርግ በመንግስተ ሰማይ ከሁሉ እንደሚበልጥ ተናገረ። በምሳሌ መፅሐፍ የሰው ኩራቱ ውርደቱን ቀድሞ እንደሚመጣ ይናገራል። ሆኖም ትሁት መንፈስ ያለው ሰው እንደሚከብር ይናገራል።

*"የሚያለቅሱ ብፁአን ናቸው፣ መፅናናትን ያገኛሉና።"*
ለሐዘናችን ምክንያት የሚሆኑ ብዙ ነገሮች በሕይወታችን ያልፋሉ። ሆኖም ፊታችንን ወደእግዚአብሔር ስናዞር እግዚአብሔር ያፅናናል። ባለመታዘዙ ምክንያት እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ሰውም ሊያለቅስ ይገባዋል።

*"ትሁታን ብፁአን ናቸው፤ ምድርን ይወርሳሉ።"*
መፅሐፍ ቅዱስ ሙሴን ትሁት ሰው ነው ይለዋል። ማንኛውም ድልና ስኬት በራሱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ የተረዳ ሰው ነበር ሙሴ።

*"ፅድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁአን ናቸው፤ ይጠግባሉና።"*
የተራብ ሕፃን ጡት እስከሚያገኝ ድረስ ያለቅሳል። እኛም እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምን እንደሆነ

እስክናውቅ ድረስ መራብ ይገባናል። መፅሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን የሚያስደስቱት ነገሮች ምን እንደሆኑና የእኛም መንፈሳዊ ምግብ ምንጩ ይኸው እንደሆነ ይነግረናል።

***“የሚምሩ ብፁአን ናቸው፤ ይማራሉና።”***

የሚምር ሰው ርህሩህና ይቅር ባይ ነው።  እንዲህ አይነት ሰው ሌሎችን መጥላት አይችልም። ይልቁንስ የሰዎችን በጎ ገፅታ ያያል እንጂ!

***“ልበ ንፁሐን ብፁአን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና።”***

አእምሮአችንን በጥሩ አስተሳሰቦች የምንሞላው ከሆነ ንፁሕ ልብ ሊኖረን ይችላል። የአለምን ቆሻሻ ነገሮች የምናደምጥ ከሆነ ግን ልባችንና አእምሮአችን ይቆሸሻሉ፣ ይረክሳሉም። ስለምናነበው፣ ስለምናየውና ስምንሰማው ነገር እጅግ አብዝተን ልንጠነቀቅ ይገባናል።

***“የሚያስራርቁ ብፁአን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።”***
ሰዎች እንዲግባቡና ወዳጆች እንዲሆኑ ታበረታታላችሁ?  እንዲህ አይነት ሰዎች ከሆናችሁ አስታራቂዎች ወይንም የሰላም ሰዎች ናችሁ።
ሰላምን በተመለከተ ለአንድ ችግር መንስኤ ወይንም የመፍትሄው አካል ልትሆኑ ትችላላችሁ። ምርጫችሁ የትኛው ነው? የሰላም ሰዎች ሁኑ።

***“ስለ ፅድቅ የሚሰደዱ ብፁአን ናቸው፤ መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።”***
ምንም እንኳን ሌሎች ሰዎችን ቢያስቆጣና ቢያበሳጭም ሁልጊዜ ትክክለኛ የሆነ ነገር መርጠን መያዝ ይገባናል። አንዳንድ ጊዜ እንዲህ አይነት ነገር ማድረግ ከባድ ነው፤ እግዚአብሔርን ግን ደስ ያሰኘዋል።

*እነኝህ የብፅእና ስብከቶች የሚገኙት በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 5፡ 1 – 12 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com